ኢትዮ-ፓረንትስ ት/ቤቶች አዲስ አበባ (ገርጂ፣ ጉለሌ)ና ሐዋሳ

Fax: +251-116-295034 Gullele (A.A) +251-112-593747/48

Gerji (A.A) +251-116-512325 Hawassa +251-462-22582

የስምንተኛ ክፍል መለማመጃ ጥያቄ

መመሪያ ፩፡- የሚከተሉትን የተለያዩ ጥያቄዎች እንደአጠያየቅ ባህርያቸው ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆኑአቸውን መምረጥ መመረጥ ፡፡

1. ‹‹ሰሩላቸው›› በሚለው ቃል ውስጥ በድምጾች መገራበት ሳቢያ ቅርጹን የቀየረው ፊደል የቱ ነው?

ሀ. ለ ሐ. ሉ

ለ. ሎ መ. ረ

2. ‹‹በሠፈሩት ቁና መሠፈር አይቀርም›› ለሚለው አባባል ፍቺ የሚሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የተበደሩት ይከፈላል ሐ. በተበደሩት ልክ ተሠፍሮ ይመለሳል

ለ. ያበደሩት ይመለሳል መ. ሰው የእጁን አያጣም

3. የሆነ ያልሆነውን መቀባጠር የሚለውን ሀሳብ የሚተካው አባባል የቱ ነው?

ሀ. ባፍ ይጠፋ በለፈለፉ ሐ. ለነገረኛ ጀርባህን ስጠው

ለ. የባጥ የቆጡን መለፍለፍ መ. ወሬኛ የወሰደውን ፈረሰኛ አይመልሰውም

4. መጠንሰሻው ሎሚ ማጠቢያው እምባጮ፣

የነገሊት ጠላ እንዴት ነህ መረጮ፡፡ ግጥሙ የትኛውን አይነት ጠላ ያመለክታል?

ሀ. በእምባጮ ታጥቦ በሎሚ ለተጠነሰሰ ሐ. አንዴ ሲጎነጩት ራስ ለሚያዞር

ለ. ከመኮምጠጡ የተነሳ ጨው ጨው ለሚል መ. መዓዛው ሎሚ ሎሚ ለሚል

5. ሰው ቃሉን ሳይጠብቅ (ዕምነት ሲጓደል) ሲቀር የሚባለው አባባል የቱ ነው?

ሀ. አገባሻለሁ ያለ ላያገባሽ ከባልሽ ሆድ አትባባሽ

ለ. ሲሰርቀኝ ያየሁትን ቢጨምርልኝ አላምነውም

ሐ. ጌታዋን የተማመነች በግ ላቷን ውጪ ታሳድራለች

መ. በሬ ካራጁ ይውላል

6. ‹‹በደንባራ በቅሎ ቃጨሞል ተጨምሮ›› ለሚለው አባባል የሚስማማው

ሀ. ያልተገራ ፈረስ ቢሄድ አያምርበት

ለ. በእሳት ላይ ቤንዚን ማርከፍከፍ

ሐ. ነገሮችን መጠን

መ. ውበትን ለማጉላት ቃጭል መጨመር

7. ይህቺ ላም ከመጀመሪያ ጀምሮ ባለመውለዷ_____ ሆናለች።

ሀ. ከሲታ ሐ. ጥገት

ለ. መሲና መ. ከበድ

8. አለሙ ስጋውን ለሚስቱ _____ አጎረሳት

ሀ. መትሮ ሐ. ከትፎ

ለ. ቆርጦ መ. ጎርዶ

መመሪያ ፪፡- የሚከተሉትን ቅኔዎች እንደአጠያየቃቸው ባህርያቸው ትክክለኛ መልስ ምረጥ/ ምረጪ።

1. መንገዱ ተሰርቷል ጭንቅም የለብን፣

ወንዙን ለመሻገር ጊቅ እያለብን ። የወርቁ ፍቺ

ሀ. ወንዙ እየሞላብን

ለ. በላያችን ላይ ምራቅን እየተፋ

ሐ. ወንዙ አላሻግር አለን

መ. ከዚህ በኃላ ጭንቅ የለብንም

2. እመንታ መንገድ ላይ አንድ ቤት ነበረኝ፣

አላፊው አግዳሚው ያፈርሰው መሰለኝ። የቅኔው ህብረ ቃል

ሀ. መሰለኝ ሐ. አላፊው አግዳሚው

ለ. አላፊው መ. ያፈርሰው

3. እረሀብ ቢጠናብን እጅግ ቢጨንቀን፣

ጎመን በልተን አደርን ያንን ቀንጥሰን ። የወርቁ ፍቺ

ሀ. ያን የመከራ ቀን አልፈን ሐ. ቆርጠን ተመገብን

ለ. <<ቀ>> ን ፊደል አውቀን መ. ከረሀባችን ታገስን

4. እንካ ብላ አለችኝ ደረቁን እንጀራ፣

እሷ በነካካው በራሰው ልትበላ። የወርቁን ፍቺ ለማግኘት የምንጠቀምበት ዘዴ

ሀ. ቃላትን በማጥበቅና በማላላት ሐ. ቃላትን በመሰንጠቅ

ለ. ታሪክን በማወቅ መ. ቃላትን በማጣመር

5. እያነጋገረ ቢጠይቀኝ ወሬ፣

አላቅም ብዬ ነው አለመናገሬ ። የወርቁ ፍቺ

ሀ. የሚችለኝ የለም ሐ. ዕውቀት የለኝም

ለ. አልናገርም መ. ባለመናገሬ ተጎዳሁ

መመሪያ ፫፡- የተጓደሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች የሚያሟሉ ቃላት ወይም ሀረጋት ምረጥ/ ምረጪ።

1. ሳይርቅ በቅርቡ _____

ሀ. ሳይደርቅ በእርጥቡ ለ. ቶሎ መመለስ ሐ. መያዝ መ. መጠንቀቅ

2. ላለፈ አይፀፀቱም _____

ሀ. ዳግም አይሳሳቱም ለ. ለሚመጣው አይበለጡም ሐ. አልፏልና መ. ለወደፊቱ ተጠንቀቁ

3. ሠርገኛ መጣ በርበሬ_____

ሀ. ግዙ ለ. ውቀጡ ሐ. ቀንጥሱ መ. አስፈጩ

5. _____ ገለባ ለከብት

ሀ. ሳንባ ለድመት ለ. አጥንት ለውሻ ሐ. ቆሎ ለተማሪ መ. ድርቆሽ ለበሬ

6. ጦር ሲመጣ _____

ሀ. ዛቢያ ፍለጋ ለ. ዛቢያ ቆረጣ ሐ. ወደ ጫካ ጉዞ መ. ሁሉም ፍርጠጣ

7. ማር ሲበዛ_____

ሀ. ይጣፍጣል ለ. ያማል ሐ. ያስጠላል መ. ይመራል

መመሪያ ፬፡- በፍቺ ልዩ የሆነው ምረጥ/ ምረጪ።

1. ሀ ሂስ ለ. ትችት ሐ. ነቀፌታ መ. ሙገሳ

2. ሀ. ዳዋ ለ. ሜዳ ሐ. አረም መ. ጢሻ

3. ሀ. ባዘራ ለ. ድንገላ ሐ. ፈረስ መ. በቅሎ

4. ሀ. ነት ለ. ቁርበት ሐ. ምንጣፍ መ. ጀንዲ

5. ሀ. ጠላት ለ. ባላንጣ ሐ. ባዕድ መ. ተቀናቃኝ

6. ሀ. ቧልት ለ. ምር ሐ. ፌዝ መ. ዋዛ

7. ሀ. እክል ለ. ችግር ሐ. ሳንካ መ. እብለት

8. ሀ. ዘብጥያ ለ. ሸንጎ ሐ. ወህኒ መ. እስር ቤት

መመሪያ ፭፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች እንደአጠያየቅ ባህርያቸው ትክክለኛ መልስ ፃፍ/ ፃፊ፡ **Y**

1. የጊዜ አይነቶችን በመዘርዘር ለእያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ምሳሌ በመስጠት አብራራ/ አብራሪ፡

_____

_____

_____

_____

_____

_____

2. ‹‹ቤታችን›› በሚለው ቃል ውስጥ ያለው መድረሻ ቅጥያ ‹‹-ኣችን›› ምንን ለማመልከት እንደገባ ግለጪ/ ግለፅ።

3. ‹‹የታጠበው ልብስ›› የስም ገላጩ የተመሰረተው ከ_____ ነው።

4. ቃለ መጠይቅ ከመደረጉ በፊት መከናወን ያለባቸውን ተግባራት ዘርዝሪ/ ዘርዝር።

5. የውይይት አቀራረብ መመሪያ ከሆኑት ውስጥ አራቱን ጥቀስ/ ጥቀሽ።

6. በግጥምና በዝርው ፅሑፍ መካከል ያለውን ልዩነትና አንድነት አብራራ/ አብራሪ።

7. የአረፍተ ነገር ስልቶችን ከዘረዘርክ/ ከዘረዘርሽ በኋላ ለእያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ምሳሌ ስጥ/ ስጪ።

8. ጥገኛ መስተዋምር ማለት ምን ማለት ነው?